የሰ.መ.ቁ. 180551

ህዳር 28/2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- መዓዛ አሸናፊ

እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

አመልካች፡- ሀዊ ሁንዴ

ተጠሪዎች፡

1. አምበሳ አዱና
2. አዱና ኢ.ዴሳ
3. ዱ.ዴሳ አያኖ
4. ውሌሳ ለታ
5. ሻምቦ ውሌሳ
6. ታደሰ ውሌሳ
7. በንቲ ለታ
8. እናኑ ጉሬጃ
9. ዳባ ለታ
10. ጫልቺሳ እናኑ
11. ሂርጴ ሰርዳ
12. ገሸማ ጉሬጃ
13. በዳዳ በንቲ
14. ትርፌሳ ገሸማ
15. ኢ.ጃራ ለታ
16. ፉፋ ጣፋ
17. ቶለሳ ጣፋ
18. ጃለኔ ለታ
19. ዱ.ጋሳ ውሌሳ
20. ገደፋ አዱኛ
21. አዱና ሰቦቃ
22. ኢ.ዴሳ አያኖ
23. ደበሎ ሙለታ
24. ሙለታ አዱና
25. ነገሳ ሙለታ
26. ተፈራ አያኖ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የቻለው በፍትሐ ብሔር ክስ ክርክር ተከሳሽ የነበረ ሰው በክርክር ላይ እያለ መሞቱን ተከትሎ የሚቹ ወራሾች ሚቹን አስመልክቶ የተሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 መሰረት ሊቃወሙ አይችሉም በሚል የተወሰነበትን የህግ አግባብ መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡

ጉዳዩ እንዲህ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪዎች የአመልካችን እናት ጨምሮ በሶስት ሰዎች ላይ የገጠር መሬት ይዞታን በተመለከተ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምዕራብ ሸዋ ዞን ግንደበረት ወረዳ ፍርድ ቤት ክስ ያቀርባሉ፡፡ ጉዳዩ በክርክር ላይ እያለ የአሁን አመልካች እናት ከዚህ ዓመት በሞት ይለያሉ፡፡ ክርክሩም በዚሁ ቀጥሎ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የአሁን አመልካች ከእናታቸው አኳያ የተሰጠው ውሳኔ መብታቸውን የሚነካ መሆኑን ጠቅሰው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 መሰረት የመቃወም አቤቱታ ውሳኔን ለሰጠው ወረዳ ፍርድ ቤት ያቀርባሉ፡፡ ፍርድ ቤቱም በመቃወም አቤቱታው ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ክርክር የቀረበበት ይዞታ የአሁን አመልካች እናት እና አባት መሆኑ እና በስማቸውም ተመዝግቦ የሚገኝ ስለመሆኑ አረጋግጫለሁ በሚል ምክንያት ቀድሞ የተሰጠውን ውሳኔ ሽሯል፡፡ በዚሁ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ ውሳኔን አፅንቷል፡፡

የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ በመ/ቁ/305233 ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ሐምሌ 02/2011 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ አመልካች የመቃወም አቤቱታ ባቀረቡበት ጉዳይ ላይ የአመልካች እናት የክርክሩ ተካፋይ ሆነው በክርክር ላይ እያሉ ከሞቱ አመልካች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 50 በሚያዘው መሰረት በእናታቸው እግር ተተክተው ክርክሩን ከሚያስቀጥሉ በቀር በሚያውቁት ጉዳይ ላይ ውሳኔውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 መሰረት ሊቃወሙ አይችሉም በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ውድቅ አድርጓል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ሐምሌ 05/2011 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም የአሁን ተጠሪዎች ክርክር የተነሳበት ይዞታ ይገባናል የሚል መከራከሪያ ከማቅረብ ባለፈ አመልካች በመቃወም አመልካችነት ቀርባ ልትከራከር አይገባም የሚል ክርክር ባላቀረቡበት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ባልተነሳ ጉዳይ ላይ ውሳኔ መስጠቱ አግባብ አይደለም፤ ወላጅ እናት ከተጠሪዎች ጋር በክርክር ላይ የነበሩ ስለመሆኑ የማውቀው ነገር የለም፤ እናቴ በክርክር ላይ እያሉ ሞሞታቸውን ፍርድ ቤቱ

ከተረዳ ከእርሳቸው አንፃር ጉዳዩን ማቋረጥ ሲገባው ክርክሩን ቀጥሎ በተጠሪዎች ማስረጃ ብቻ ውሳኔ መስጠቱ ከሥነ ሥርዓት ውጭ በመሆኑ እና የስር ፍርድ ቤቶች ከዚህ አኳያ ስህተቱን አርመው የሰጡትን ውሳኔ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች የውርስ ሀብቱን ለመጠየቅ መብታቸው የሚቋቋመው እናታቸው ሲሞቱ ሆኖ እያለ የአሁን ተጠሪዎች ከአመልካች እናት ጋር ሲከራከሩ አመልካች ታውቅ ነበር በሚል ምክንያት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 ያቀረቡትን መቃወሚያ ውድቅ ያደረገበት አግባብ ለዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

በዚሁ አግባብ 24ኛ ተጠሪ መሞታቸው በመረጋገጡ ምክንያት ከእኚህ ተጠሪ ውጭ ያሉት ተጠሪዎች በጠበቃቸው አማካኝነት ጥር 14/2012 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ ባቀረቡበት ጉዳይ ላይ ወላጅ እናታቸው በተከራካሪነት ተካፋይ የነበሩ ስለመሆኑ እና ሌሎች ተከሳሾች የነበሩትም የአመልካች ወንድሞች በመሆናቸው አመልካች ክርክሩን ታውቅ ነበር፣ አመልካች በክርክሩ ተካፋይ መሆን የሚፈልጉ ከሆነ አንድም በክርክር ላይ እያሉ በሞቱት እናታቸው እግር ተተክተው ክርክሩን ማስቀጠል አልያም ከውሳኔው በኋላ ቅሬታ ካላቸው በይግባኝ ከሚያሳርሙ በቀር መብቱ በውርስ እንደተላለፈላቸው ወራሽ ሳይሆን መብቱ እንደተነካ 3ኛ ወገን ሆነው በፍርድ ተቃዋሚነት ሊቀርቡ አይችሉም፣ ወሳኔውም በአፈፃፀም ያለቀ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 መሰረት መቃወሚያ የሚቀርብበት ባለመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት ነጥብ የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር ቅሬታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የቀረበውን ክርክር ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በመሰረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ጥር 358 መሰረት የፍርድ መቃወሚያ ማቅረብ የሚችለው ቀድሞ በተደረገው ክርክር የሙግቱ አካል ሊሆን ይችል የነበረ ሆኖ እርሱ ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር በተሰጠው ውሳኔ መብቱ የሚነካ ሶስተኛ ወገን ነው፡፡ አንድ ሰው ወይም አካል በፍርድ ቤት በተያዘ ክርክር የክርክሩ አካል ሊሆን የሚችለው በፍርድ ቤት በሚሰጥ ትዕዛዝ፣ በራሱ በጣልቃ ገብ አቤቱታ አቅራቢነት አልያም በተከሳሽ ወገን ጥያቄ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 40፣ 41 እና 43 ድንጋጌዎች ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ ከእነዚህ በሂደት ላይ በሚገኝ ሙግት መግቢያ መንገዶች ውስጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ጥር 358 መሰረት በፍርድ ተቃዋሚነት ሊቀርብ የሚችለው

በዋናነት ቀድሞ በተደረገው ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 41 በተመለከተው መሰረት በጣልቃ ገብነት ቀርቦ መብቱን እና ጥቅሙን ማስከበር ይችል የነበረ ሶስተኛ ወገን ነው፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካች ውሳኔ ያረፈበት ይዞታ የግል ይዞታዬ ነው በሚል ሳይሆን ከወላጅ እናቴ በውርስ ሊተላለፍልኝ የሚገባ ሀብት ነው የሚል ነው፡፡ አውራሻቸው የሆኑት ወላጅ እናታቸው ደግሞ ይህንን ይዞታ በተመለከተ በአሁን ተጠሪዎች ክስ ቀርቦባቸው በክርክር ላይ እያሉ ስለመሞታቸው የተካደ አይደለም፡፡ ጉዳዩ ይህ ከሆነ ለክርክር ምክንያት የሆነውን ይዞታ በተመለከተ አመልካች የሚኖራቸው መብት ከአውራሻቸው የተላለፈላቸው እንጂ እራሱን የቻለ መብት ባለመሆኑ ወላጅ እናታቸው ተካፋይ ለነበሩበት ክርክር 3ኛ ወገን የሚባሉ አይደለም፡፡ ቀድሞ በተደረገ ክርክር እና በተሰጠ ውሳኔ 3ኛ ወገን ያልሆነ ሰው ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 መሰረት በፍርድ ተቃዋሚነት የሚመጣበት የህግ አግባብ የለም፡፡ የአመልካች ጉዳይም በክርክር ላይ እያለ የሞተን ተከሳሽ መብት የሚመለከት በመሆኑ ጉዳዩ የሚመራው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 50 እና ተከታዮቹ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት አመልካች በክርክር ላይ የነበሩት ወላጅ እናቴ ከሞቱ በኋላ ወደ ክርክሩ እንድገባ እና የክርክሩ አካል እንድሆን ለሟች ወራሾች ተገቢው መጥሪያ አልተደረገም የሚል መከራከሪያ በአመልካች በኩል አልቀረበም፡፡ ይህ ባልሆነበት አመልካች አውራሻቸው ተከራካሪ በነበሩበት ጉዳይ ላይ በፍርድ ተቃዋሚነት ቀርበው የሚከራከሩበት የህግ አግባብ ባለመኖሩ የክልሉ ሰበር ችሎት የደረሰበት ድምዳሜ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/305233 ሐምሌ 02/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ